

MONTGOMERY COUNTY PUBLIC SCHOOLS

# ቅድመ-ሙአለህፃናት/ሄድ ስታርት የተማሪ ምዝገባ

MONTGOMERY COUNTY PUBLIC SCHOOLS በካውንቲው ከዳር እስከ ዳር በሚገኙ ት/ቤቶች የገቢ ብቃት ላላቸው ቤተሰቦች ነፃ የቅድመ-ሙአለህፃናት እና የሄድ ስታርት ፕሮግራሞች ያቀርባል። እነዚህ ፕሮግራሞች ልጆች ለሙአለህፃናት ዝግጁ ለመሆን የሚያስፈልጓቸውን ክሂሎቶችና እውቀት ይሰጣሉ።

- Rocking Horse Road Center (የመመዝገቢያ ቦታ)
  4910 Macon Road
  Rockville, Maryland 20852
  ሰኞ–አርብ 9:00 a.m.–4:00 p.m.
  ዘው ብሎ መግባት ይቻላል
  ከተፈለገ ቀጠሮዎች ማስመዝገብም ይቻላል

## የ4 ዓመት ልጅ አለዎት?

## አዎን ከሆነ፣

ቤተሰብዎ በMCPS ለነፃ የቅድመ-ሙአለህፃናት ወይም የሄድ ስታርት ፕሮግራሞች ብቃት ሊኖረው ይችላል።

## የማስመዝገብ ሂደቱን ለመጀመር በ301-230-0676 ይደዉሉ

### ደረጃ 1

**መግባት**

- የገቢ መመሪያዎችን ማሟላትዎን ይወቁ/ይጠይቁ

301-230-0676 ይደውሉ

ሲያመለክቱ፣ ሰራተኛዉ/ስታፍ፡-

- የተማሪንና የወላጅን ማንነት ያረጋግጣል/ታረጋግጣለች
- የካውንቲ ነዋሪነትን ያረጋግጣል/ታረጋግጣለች
- የቤተሰብ ገቢን ያጣራል/ታጣራለች

### ደረጃ 2

**የክትባት መስፈርቶች**

- የጤና ፓኬት ይቀበላል/ትቀበላለች
- ተማሪው/ዋ ት/ቤት ከመግባቱ/ቷ ቀደም ብሎ/ላ የአካል/የጤና ምርመራና አፈላጊ የሆኑ ክትባቶችን መጨረስ ያስፈልገዋል/ያስፈልጋታል።

### ደረጃ 3

**የቤት ጉብኝት ወይም የመምህር/ አስተማሪ ስብሰባ**

- የጤና ፓኬቱን መስጠት
- መምህር ስለ ትምህርት ክፍለ ግዜዎችና አውቶብስ መጓጓዥያ መረጃ ይሰጣል/ትሰጣለች።

### ደረጃ 4

**ት/ቤት መገኘት**

- ማጓጓዥያ አውቶቡስ ይቀርባል።
- ተማሪው/ዋ እለታዊ የክፍል ትምህርቶች ከሰኞ እስከ አርብ ይከታተላል/ትከታተላለች።

ይቀጥላል

# የምዝገባ ማስረጃዎችና በብዛት አገልግሎት ላይ የሚውሉ ሰነዶች

## የተማሪ እድሜ

### ለት/ቤት ብቁ ለመሆን፡-

- ተማሪዎች እስከ ሴፕቴምበር 1 ድረስ 4 መድረስ አለባቸው።

#### ምሳሌዎች

- የልደት ምስክር ወረቀት
- ፓስፖርት/ቪዛ
- የሆስፒታል ማስረጃ
- የሃኪም ምስክር ሰነድ
- የቤተክርስቲያን ምስክርነት ሰነድ
- የወላጅ በህግ የተመዘገበ የመሃላ ቃል (የትውልድን ቀን ትክክለኛነት በማረጋገጥ በህጋዊ ቃል ተቀባይ የተመሰከረ ቃል)
- ሌላ ህጋዊ ወይም በህጋዊ ቃል ተቀባይ የተመሰከረ ማንነት

## ተማሪውን/ዋን አስመዝጋቢ ሰው ማንነት/መለያና ከተማሪው/ዋ ጋር ያላቸው ዝምድና

- መታወቂያ እና
- ከተማሪ ጋር ስላለ ዝምድና ማስረጃ
- ሌሎች ጉዳዮች፣ ተገቢውን ፎርምና የሚያስፈልገውን ሰነድ ለመወሰን ከሰራተኞች/ስታፍ ጋር አብረው ይስሩ

#### ምሳሌዎች

- ፎቶ ያለበት የመንጃ ፈቃድ መታወቂያ
- ፓስፖርት፣ የውጭ ዜጋ የቋሚ ነዋሪነት ማረጋገጫ ካርድ ፣ የዜግነት ሰነዶች
- የፍርድ ቤት ትእዛዝ
- የመለያየት ወይም የፍች ህጋዊ ማስረጃ
- በህጋዊ ቃል ተቀባይ የተመሰከረ የወላጅ ቃለ መሃላ (ዝምድናውን በመረጋገጥ በህጋዊ ቃል ተቀባይ ፊት የተከናወነ መሀላ)

## በMontgomery County ነዋሪነት

### የመኖርያ ቤት ባለቤት

- ወቅታዊ የንብረት ግብር ማስከፈያ/ቢል ቅጂ ማቅረብ

### ተከራይ

- የወቅታዊ ኪራይ ውል ቅጂ ማቅረብ

### የደባል ቤት

- ከቤት ባለቤት ወይም ከተከራይ ሰነድ ማቅረብ

### ቤት-የለሽ

- ከቤት አልባ አገናኝ ጋር መስራት

#### ምሳሌዎች

- የህክምና ሂሳብ/ወጭ
- የመኪና ምዝገባ
- የመኪና መድህን ውል/ቢል
- ወቅታዊ የውሃ/ኤሌክትሪክ/ጋዝ ማስከፈያ ቢል
- ወቅታዊ የቴሌፎን ማስከፈያ ቢል
- የአድማጭ/መራጭ መመዝገቢያ ካርድ
- የUSCIS ማመልከቻ
- የመንግስት ወይ የኦፊሴል ደብዳቤ ልውውጥ በመኖርያ አድራሻ

## የቤተሰብ ገቢ ማረጋገጫ

- ቤተሰብ ለሁሉም አዋቂዎች ወቅታዊ የገቢ ማረጋገጫ ማቅረብ ይኖርባቸዋል

#### ምሳሌዎች

- የመጨረሻዎቹ የሦስት ክፍያዎች ማስረጃ
- የአሁኑ የአገርውስጥ ገቢ ፎርም
- የቅጥር ደብዳቤ
- የሥራ አጥ ጥቅማጥቅሞች
- በህግ የተረጋገጠ የገንዘብ ድጋፍ ደብዳቤ
- የTemporary Cash Assistance (ግዚያዊ የጥሬ ገንዘብ ድጎማ) (TCA) ክፍያዎች

0618.17 Amharic • EGPS • 500